# “እኩል ደራ ደራ
# ከነ‘ሜቴ ጋራ!”

*መዝገቡ ሊበን*
*ከሚነሶታ*

ገጣሚና ደራሲ....
ከግዑዙ መሬት፣ ከመንደሩ ይልቅ ከዘር ማንዘሩ፣
ሰብዓዊነትን ያልማል ብዕሩ
“የሰው ልጅ ልብ...” ነው አገሩና ድንበሩ!
ሰብዓዊነት ነው ክብሩ፤
            ገጣሚ አገር የለውም፣
            “ዩኒቨርሱ”ም አይበቃውም፤
ሰዋዊ ህመም ያመዋል፣
ፈውሱም ይፈውሰዋል፣
ገጣሚ ያ ይበቃዋል!
            ወርዶ ወርዶ “ቀየ መንደር ውስጥ አይወድቅም”
            አዎ! ገጣሚ፣ ደራሲ እንዲያውም አገር ***የለውም፣***
            የበዓሉ አገሩ ሰው ***ነው፣***
“...ህንጻው ምን ቢረዝም፣ ምን ቢጸዳ ቤቱ፣
መንገዱ ቢሰፋ ቢንጣለል አስፋልቱ፣
ሰው ሰው ካልሸተተ ምንድነው ውበቱ፣
የኔ ውብ ከተማ የኔ ውብ አገር፣
የሰው ልጅ ልብ ነው የሌለው ድንበር...” (አሮማይ)
            ጸጋዬም ጊንጪ ኢምንት ቢሆንበት
            ጉደር፣ አምቦ፣ ቡራዩ ... ጠ’ቦበት፣
            አዲሳ’ባ ኢትዮጵያም ብታንስበት፣
      ብዕሩ ፈርዖኑን ተመኘ፣
      ነፈርቲቲ እና አፍሮዳይትን ቃኘ፣
ገጣሚ አገር የለውም፤
“ዩኒቨርስ”ም አይበቃውም!
ደራሲ እና ገጣሚ እንዲህ ጠ‘ቦ አይጠብም፣
ከቶ አገር የለውም.....
      ወለላዬ ግሩም ብሏል ይመስለኛል፣
      “አለ ሙያቸው ሙያ እየጫንባቸው...”


Henoke Yeshetlla
Thursday at 5:45 PM ·

ካልተወሰነ ጊዜ «Good bye Facebook...» ተስፋ ቆርጠን ሳይሆን በተስፋቢሶች ኩሸት ተሰላችተን!!! Good bye Facebook.ተሸንፈን ሳይሆን ፥ ተንሻፎ ከቆመ ጋ ስለ ከግካጋነት ማውራት ቢታክተን !!! Good bye Facebook••• የምንታገላቸው ልንፀልይላቸው የሚገባ ህሙማን መሆናቸውን ስለተረዳሁ ብቻ ሳይሆን ፥ የማየው ነገር ስለማይመጥነኝ! Good bye Facebook.••• ሀሳብን በሃሳብ መሞገት የሚችል ትውልድ እስቲመጣ፥ ሰው በሃሳቡ ሃሳቡ እንጂ ማንነቱ የማይዋረድበት ዘመን እስኪይ፥ ከሰውነትህ የፖለቲካ ድርጅት አባልነትህ የሚበልጥባቸው ታጋዮች ረግፈው እስኪያልቁ••• እነ ዩሃንስ አድማሱን የበላ ህዝብ ፥ እነ ፀጋዬ ገብረ መድህንን ስልቅጥ አድቆ የዋጠ ማህበረሰብ ፥ እነ በዓሉ ግርማን ያነከተ ህዝብ ፥ እነ አቤ ጉበኛውን የጎረሰ ህዝብ ፥ እነ አስራት ወልደየሰን ከርትፎ የበላ ህዝብ ፥ ይህ እንጦሮጦስ ሆዱ ተላውሶ እውነት እስኪያስታውከው Good bye Facebook!

ኄኖክ የሺጥላ